# ለዶ/ር ጌታቸው በጋሻው ኢሜል ምላሽ

(ነሲቡ ስብሐት (አሉላ) ግንቦት 7 ቀን 2007 ዓ.ም.)

***ሚያዝያ 30 ቀን 2007 ዓ.ም. "ዝናብ አይፈሬ ታጋዮች"*** (http://ethiopia.org/files/ZenabAyefere_Tagayoch.pdf) **በሚል ርዕስ ባስነበብኩት ጽሁፌ ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው የተሰማቸውን በግል ኢሜል አድርገውልኛል። አድርገውልናል። አድርገውልናል ያልኩት እኔም እሳቸውም በጋራ ለምናውቃቸው ሲሆን የመልዕክታቸውም ርዕስ "Your garbage on Aiga Forum" በሚል ነው። ይህንን *"ወያኔ ነህ"* የሚል መልዕክታቸውን እኔም በጋራ ለሚያውቁን ጥቂት ወገኖች ልኬ ከአንድ ወገን ጋር መለስተኛ መፃፃፍ ተካሂዷል። ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው በዚህ መልዕክታቸውና በተከታታይ በፃፉት ሁለት ምላሾች አሁንም ጉዳዩ መታወቅ አለበትና ለአንባቢና ለኢትዮጵያ ሕዝብ አቅርቤአለሁ።**

# Your garbage on Aiga Forum

Wednesday, May 13, 2015 1:33 PM

From:

"Getachew Begashaw" <getachew.begashaw@yahoo.com>

To:

"Fikuru Kidane" <fikurukid@yahoo.com> "Alulla Nega" <alulla2@yahoo.com>

Ato Fikru and Allula,

I found the heap of lies and garbage you have insidiously and maliciously piled on me in the centerfold of Aiga Forum (the TPLF website with red prints for that matter-- ). Indeed, you belong there, and I am very happy for you to have found your final address. Congratulations!!

Here is the link for you in case you need some help:
http://aigaforum.com/article1/050715_ZenabAyefere_Tagayoch.pdf

**ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው እንደማንኛውም ሰው ትላንትም ዛሬም ወደፊትም ማከብራቸው ናቸው። ይህ ማለት ግን እንደ ፖለቲከኛ በሀገርና ሕዝብ ጉዳይ ላይ በሚሰጡት አስተያየትና በሚወስዱት አቋም ሌሎች ከእሳቸው ጋር የሀሳብ ልዩነት እንደሚኖራቸው ሁሉ ሊኖረኝ ይችላል። ምናልባት የእኔ ለየት የሚለው እንደ እውቅናችን፣ እንደቀረቤታችን አይቶ እንዳላየ፣ ሰምቶ እንዳልሰማ አለመሆኔና ማንነቴን ሳልደብቅ በመፃፌ ሊሆን ይችላል። እሳቸው በአመኑበት ጉዳይ በግልጽ በአደባባይ እንደሚናገሩና እንደሚጽፉ ሁሉ ከበስተጀርባ ሆኜ ላብጠለጥላቸው ፍላጎቱም የለኝ። በሌላም በኩል እየሄዱበት ያለው አቅጣጫ ልክ አይደለም ብዬ ከራሳቸው አንደበትና አምስት ጣታቸው ከጨበጠው ብዕር እያጣቀስሁና እያመሳከርሁ ነው ያቀረብሁት። የማቀርበው።**

ዶ/ር ጌታቸው በፃፍኩት ጽሁፍና በለቀኩት የአምስት ደቂቃ የትላንትና የዛሬ አባባላቸው ላይ (ለማድመጥ ከፈለጉ ከታች ይጫኑ)

(http://ethiopia.org/plugins/content/nmapp/popup.php?cfg=54o2q2n2r2x304r4z2n254v57486h4r55406r4z3l5j4h47664v2o296w2t41456g4s5f58494p4p2j4v5x2p264l406u59405j2m2e4z204q2v3t2v3w2v364m2t27644u4p296w2t4o256w26424t4x2y4u2u276z2u474o4z526n4l4t4t2a6v2d4q256z2a4&url=eNortjK0UtJXsgZcMAkSAcc,&plw=250&plh=170&bgc=000000&tit=My%20cool%20player )

የተሳሳትኩት ካለ፣ እሳቸው እንደሚሉት "*Copy & Paste*"/ "*ኩርጆ መለጠፍ*" በማድረግ የተቀነባበረም ከሆነ ጉዳዩን በማሳየትና በማጋለጥ ማቅረብ ይችላሉ። በሌላም በኩል እየሄዱበት ያለውን የሰሞኑን ከሻቢያ ጋር እንሥራ ጉዳይ ለእኔና ለሌሎችም ግልጽ ያልሆነ ጉዳይ አብራርቶ በመፃፍ ማስረዳት ሲገባቸው ዘለፋና ስድባቸው ከአላቸው የዕድሜ ተመክሮና ትምህርት ደረጃ አንጻር የሚጠበቅ አይደለም።

በሙያቸው ከሚያበረክቱት ግልጋሎት በተጨማሪ የዩንቨርስቲ መምህር የሆኑት ዶ/ር ጌታቸው ስንቱን በየቀኑ እያስተማሩ እያለ እኔን አንድ ሀሳቤን የወረወርኩ ኢትዮጵያዊ ማስተማር እንዴት አቃታቸው? ለምን ሻቢያን ተቃውመህ ጻፍክ ተብሎ ***"ተንኮል ያዘለ መርዘኛ አዕምሮ"*** ይባላልን? ወያኔና ሻቢያ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው እንዴት ይባላል ተብሎ ***"የተዋረደ፣ እያደፈጠ ያለ ስም አጥፊ"*** የሚሉ ቃላቶች ለሀሳብ ልዩነት መልስ ናቸውን?

ከዶ/ር ጌታቸውም ሆነ ከግንቦት 7 በኢትዮጵያ ሀገራችን ጉዳይ ያለኝ ልዩነት መሠረታዊ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ በቀጣዩ መንግስት ለማንም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሙሉ የዴሞክራሲ መብቱ ሊጠበቅለት ይገባል ባይ ነኝ። ደርግ *"ኢትዮጵያ ትቅደምን እስካልተቃወመ ድረስ"* እያለ ደርጉ ውስጥ ያሉትን ሳይቀር የሀሳብ ልዩነት ያላቸውን ሁሉ ቅጥያ ስም እየሰጠ ገድሏል። ወያኔ *"ሰላምና መረጋጋት"* አሁን ደግሞ *"አሸባሪ"* በማለት ቅጥያ እየሰጠ የተቃወመውን ሁሉ ደብዛ እያጠፋና በየእስር ቤቱ እያጎረ ይገኛል። የነዚህ በባህሪ አንድ የሆኑ አገዛዞች እንደፈለጋቸው እረግጠው ሊገዙ ውይይት፣ ሃሳብ ልዩነት፣ ተቃዋሚ የሚል ነገር ሊሰሙ አይፈልጉም። ለዚህም ነው ወያኔ ከህዝብ መከራ አንፃር ቀጣይ የደርግ አገዛዝ የሚባለው።

በቀጣይነት ሀገርን የሕዝብና የልጆቿ እናደርጋለን፣ በሀገራችን የዴሞክራሲ መብት እንዲሰፍን እንታገላለን የሚሉ ኃይሎች ታዲያ ገና ስልጣኑን ሳይዙት *"ልክ አይደለም፣ አካሄዳችሁ አጉል ነው!"* ብዬ ሀሳቤን ለአንባቢና ለወገን ባቀረብሁ ***"ወያኔ፣ መሰሪ፣ መጥፎ፣ እንደጠላት መታየት ያለበት ወዘተ."*** እየተባለ በእንግሊዘኛው መዝገበ ቃላት ላይ ያሉ የስድብ ቃላት ምላሽ እውን ገፀ በረከትና አስተማሪ ይሆናልን?

ዶ/ር ጌታቸውም ሆኑ ግንቦት 7 የሚያመቻቸውን የትግል አቅጣጫ ሊከተሉ ይችላሉ፣ ከፈለጉት ጋር ግንባር ሊፈጥሩ ይችላሉ። ግና የሚታገሉት ለሀገርና ሕዝብ እስከሆነ ድረስ ደጋፊ እንዳላቸው ሁሉ ተቃዋሚ እንደሚኖራቸው መቀበል ይኖርባቸዋል። *"እኛ ያልነው ብቻ ትክክለኛ መንገድ ነው"* ብሎ ሌላው ላይ ለመጫን መሞከር አግባብነት የለውም፤ ተቀባይነትም አያገኝም። እና በቅርቡ በፃፍኩት አስተያየቴ ዶ/ር ጌታቸውም ሆኑ ሌሎች

ሀሳብን በሀሳብ መመለስ ሲገባቸው *“እንዴት ተደፍሪ”* የሚል ኢሜላቸው ዳግም ስህተት መሆኑ ይታወቅልኝ ዘንዳ አያይዤ አቅርቤሃለሁ። ይህ ለዶ/ር ጌታቸው ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ድርጅቶችም ሆነ ግለሰቦች በፖለቲካው መድረክ ላይ እስካላችሁ ድረስ ማንም ደግፎም ሆነ ተቃውሞ ሊያቀርብባችሁ፣ ሊጽፍባችሁ ይችላል፤ ስለዚህ አስተማሪነቱና መልዕክቱ ለሌሎችም ነውና ያቀረብኩትን አንብቡ።

በወያኔ እሥር ቤት እየማቀቀች ያለችው ርዕዮት ዓለሙ እኮ “*ለምን ጻፍሽ፣ ለምን ሃሳብሽን ገለጽሽ”* ተብላ ነው። እስክንድር ነጋ ወያኔ እስር ቤት የሚማቅቀው እኮ ወያኔ ላይ ጥይት ተኩሶ ሳይሆን *“ለምን ብዕር አነሳህብን”* ተብሎ ነው። በቅርብ አምስት ጣቶቹ በወያኔ ካቴና የተከረቸሙት ተመስገን ደሳለኝ እኮ የብዕር ጥይቱን በመተኮሱ ነው። እንግዲህ ለነኚህ ወገኖች መብት የምንሟገትና የምንጮህ ወገኖች እንደ ዶ/ር ጌታቸው አሉላ/ነሲቡ እንዴት ጽፎብኝ/ጽፎብን ተብሎ ***“እንደ ወያኔ ጠላት ጎራ እንክተተው”*** ሲባል ነገ ሥልጣን ቢይዙ ወየው ለርዕዮት ዓለሙ፣ ይብላኝ ለእስክንድር ነጋ፣ አወይ ለተመስገን ደሳለኝ ወዘተ አልኩ። እኔስ ዕድሜዬን ገፍቼዋለሁና ለቀጣይ የኢትዮጵያ ልጆች ቀጣይ መከራ አዘንሁ።

ዶ/ር ጌታቸው በመጀመሪያ ኢሜላቸው የፃፍኩት ጽሁፍና የአምስት ደቂቃው የድምጽ ቅጂ ለምን አይጋ ፎረም ላይ ተለጠፈ ብለው ***“ቤትህን አገኘሁት፣ አንት ወያኔ”*** መልዕክታቸው ዝም ማለቱ ቢበቃም፤ ማንም በሀገራችን ፖለቲካ ጉዳይ ጽሁፍ የሚያቀርብ የፖለቲካ ድርጅት፣ ሲቪክ ማህበራት፣ ግለሰቦች ወዘተ የሚያስተላልፉት መልዕክት ለወዳጅ ብቻ ሳይሆን ለሚታገሉት ጠላትም እንዲደርስ ማድረግ አግባብ ነው። ያ የደረሰው ክፍል በዛሬ ሥልጣኔ በድረ ገጹ ቢለጥፈው፣ በሬድዮ ቢያስነብበው፣ በፓል ቶክ ቢወያይበት፣ በቴሌቪዥን መስኮት ቢያቀርቡት መልዕክቱ ለሕዝብ የመዳረስ አድማሱን ያሰፋዋል እንጂ ምንም ችግር አለው ብዬ አልገምትም። በሌላ በኩል ደግሞ ጠላት እርስ በርሳችን በምናደርገው መናቆር እስከተመቸው ድረስ የቅራኔውን ግለት ማባባስ አንዱ ዘዴው ነውና እንደሚጠቀምበት እንወቅ። ያውም የፃፍኩት ጽሁፍ ***<u>በሀገራችን ከእምዬ ኢትዮጵያ አንፃር የወያኔንና ሻቢያን የጋራ ጠላትነት ላይ ነው ያተኮርኩት።</u>*** እና ዶ/ር ጌታቸው ለፃፍኩት ጽሁፍ ምላሽ ካልቻሉ ***“ወደ ክስ እሄዳለሁ”*** ፉከራውን ይተዉትና ዝም ቢሉ ይመረጣል። ዛሬ እዚህ አሜሪካ በየጋዜጣውና በየሚዲያው በየጊዜው የሚብጠለጠለውን ፕሬዘዳንት ኦባማ በአለበት ሀገር ***“አሉላ/ነሲቡ ሀሳቤን ተቃውሞ ስሜን አጥፍቷልና ወደ ሕግ መቅረብ አለበት”*** ሲሉ ለእኔ “*አትናገሩ*ግ” ማስፈራሪያ ከሆነ እነሆኝ ድጋሚ ጽፌሃለሁ።

**በ Aigaforum የተለጠፈው በዚህ መልኩ ነበር**

**http://aigaforum.com/article1/050715_ZenabAyefere_Tagayoch.pdf**

**ዝናብ አይፈሬ ታጋዮች**

**(Comment on Dr Getachew Begashaw Latest Political Stand!)**

(አለሊ ሚያዝያ 30 ቀን 2007 ዓ. ም.)

We always wonder what the fate of Ethiopia would have been had EPRP not TPLF/EPRDF was victorious. And every day we are getting a clue as to what could have been its fate. Listen to Getachew's comment on Shaibya then and now

((**Comment**))

and judge for yourself as to what was Ethiopia's future with such leaders at the top! We really thought Getachew's brand of EPRP in diaspora was better choice between the two EPRPs but we were wrong...if we were to be cornered to choose between the two we would choose the other EPRP. What happen to him really?

Source = http://www.assimba.org/Articles/050715_ZenabAyefere_Tagayoch.pdf

**በዚህ የመጀመሪያ ኢሜል ያልገባኝ ጉዳይ ቢኖር ዶ/ር ጌታቸው የጽሁፉ አቅራቢና ተጠያቂ ሙሉ በሙሉ እኔ በአሉላ ስም የለቀቅሁት ነሲቡ ስብሐት ስሆን ለምን አቶ ፍቅሩ ኪዳኔን (ባልሳሳት አንጋፋውን የእስፖርት ጋዜጠኛ ሳይሆን የችካኅውን ነዋሪ ፍቅሩ ኪዳኔን ይመስለኛል) እንደጨመሩ እንቆቅልሽ ሆኖብኛል።**

*ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው በሁለተኛው ኢሜላቸው ይህንን ከመላክ በስልክ ደውለው እኔኑ ቢናገሩ ወይም ለእኔ ለብቻዬ ቢልኩ "እይ ለጊዜው በፃፍኩት ተናዶ ሊሆን ይችላልና ምንም አይደል ትንሽ ጊዜውን አሳልፌ አወራዋለሁ" ብዬ አምቄ እይዘው ነበር። ግና አሁንም የላኩላቸውን ሰዎች እንኳ "ይታዘቡኛል፣ ምን ይሉኛል?" የሚል ይሉኝታ ያጡበት የንቀት ኢሜል በመሆኑ ሌሎች ወገኖች ማየት አለባችሁና ቀርቧል። ነገ ሀገር ሊመሩና ሊያስተዳድሩ ከሚጥሩት ጋር አንዱ የሆኑት እኚህ ሰው እንዴት ተነቅፌ ብለው የፃፉትን ኢሜል አንብባችሁ "ዛሬ በዚህ በነፃው ዓለም ይህን ያሉ ስልጣን ላይ ቢሆኑ የታገሉለትን ዴሞክራሲያ መብት እውን ይለቁታል?" ብለን ጥያቄ ውስጥ ብናስገባቸው አግባብነቱ ሚዛን ይደፋል እላለሁ።*

# Re: Your garbage on Aiga Forum

From: "Getachew Begashaw" <getachew.begashaw@yahoo.com>
To: "Nesibu" <alulla2@yahoo.com>,

Subject: Your garbage on Aiga Forum
Date: Wed, May 13, 2015 10:24 PM

Dear friends,

To fully understand what this morally debauched person has written about me, I invite you to listen to my interview in its entirety. He has distorted my interview by cutting and pasting clips in such ill motivated intentions much beyond any person's belief or imaginations. If you don't want to listen to all, please tune to the footage after 24:00 minutes: http://www.ethiomedia.com/101facts/4465.html This malicious and venomous individual, who kept lurking to attack me at any given opportunity (despite my forgiveness for all the damages he had inflicted on me and the organization before) has continued to defame me in such a legally liable manner where he will have to answer in the court of law for defamation. I am just amazed for how long I have been associating with such lowly persons under the guise of this organization. These are not IHAPAS I have known, and I am thoroughly shaken to my bones to see such a wretched and very base individuals amongst us. This has never been a friend, but an enemy; and he will have to be dealt with as such.

**በአምስት ደቂቃው የድምጽ ቅጂ ያቀረብኩት ከዛሬ አራት ዓመት በፊት ዕሁድ ሐምሌ** 03 **ቀን** 2003 **ዓ.ም.** (Sunday July 10, 2011) **በቨርጅንያ ከተካሄደው የኦነግና የግንቦት** 7 **ስብሰባ በኋላ "የግንቦት 7 ንቅናቄ እና የኦነግ ስብሰባ በቨርጅንያ" በሚል ጽሁፍ ካቀረብሁ በኋላ በአሉላ አባ ነጋ ፓልቶክ ክፍል** August 14, 2011 **ቀርበው ስለ ጉዳዩ እንዲያብራሩ በተጋበዙበት ወቅት በአገኘሁት ዕድል ተጠቅሜ የጠየኳቸውን ጥያቄና የሰጡትን መልስ እንዳለ አቅርቤአለሁ። በዚያ ጊዜ ስለ ሻቢያ ያላቸውን አቋም በሙሉ ኩራት ሲናገሩ ይደመጣሉ። ከአራት ዓመት በኋላ** March 8, 2015 **በኢሳት ቴሌቪዥን የሳምንቱ እንግዳ ዝግጅት ላይ በሲሳይ አጌና ጠያቂነት የሰጡት ሁለት ክፍል ውይይት ውስጥ ስለ አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ በኢሳት ቴሌቪዥን ቀርበው የሰጡትን ቃለ ምልልስ ክፍል** 1 **አስመልክቶ** (http://ethsat.com/video/esat-bezehe-sament-dr-getachew-begashaw-march-8-2015/)

የተሰማቸውን ደስታ ያልተቆራረጠ ቅጂ አቅርቤአለሁ። (በእርግጥ አነጋገራቸው በእኔ ግምት ከልባቸው ስላልሆነ ይመስለኛል " . . . ሀ . . . ሐ . . . እ . . . ዕ . . ." ይበዛዋል)። በሌላ በኩል ከአንዱ አቋማቸው ወደ ሌላ መሸጋገሪያ ያደረኩት ከእኔ ይልቅ የራሳቸውን ድምጽ *"እንግዲህ መገለባበጥ ለአንዳንድ ፖለቲከኞች ያመቻል መሰለኝ"* ብለው ስለ ወያኔ መገለባበጥ የሰጡትን ስጠቀም *"እርሶስ?"* የሚለውን መልዕክቴን ለማስተላለፍ እንደሆነ ግልጽ ካልሆነ በድጋሚ ግልጽ ላደርግ ተገድጃለሁ። ዋናውን ቅጂ ከላይ ባስቀመጥኩት Link ከ 40ኛ ደቂቃ ጀምሮ ያለውን አድምጡና ፍርድ ስጡ።

እና ዶ/ር ጌታቸው ሻቢያን በተመለከተ ለምን የአቋም ለውጥ ሊያደርጉ እንደፈለጉ አሁንም ዘርዘር አድርገው ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ወገኖችና ለሀገራችን ሕዝብ ቢያቀርቡ ይመረጣል። በስድብ ጋጋታና በማስፈራራት አሉላን አስቆማለሁ ከሆነ ለሀገሬና ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሁንም እንደፃፍኩ፣ እንደሞገትኩ እሞታለሁ እንጂ እንኳን ዛሬ በሃምሳዎቹ ዕድሜ ወደ ሞት እየተንዝኩ ይቅርና ያኔም ገና ጨቅላ በነበርኩበት ወቅት ታንክና ክላሽ የታቀፈውን የፋሽስት መንጋና ባንዳ አልፈራሁም።

ዶ/ር ጌታቸው በሰጡት በዚህ የኢሳት ውይይት ክፍል 1 እና ክፍል 2 ልዩነቱ እራሱ በቂ ነው። ክፍል 2 የአንድ ሰዓት ውይይት ላይ ስለ ሀገሪቷ የኢኮኖሚ ሁኔታ ሲተነትኑ ለአንዲት ጊዜ እንኳ እ . . . ሀ . . . አይሉም። ከልባቸው ነዋ! የውስጣቸውን ነዋ! የክፍል 1 ውይይታቸው በተለይ ከ30ኛው ደቂቃ በኋላ ያለው እራሳቸውም ደግመው ቢሰሙት *"ምን መሆኔ ነው?"* ሊያሰኛቸው ይገባል። እኔ እዳደመጥኩት በአንድ መድረክ ሁለት ሰው ሆነው ቀርበዋል። ኢሳያስ አፈወርቂም ይህንን ሲያደምጡ በመገረም

*"ዋእ ዶክተር ጌታቸው እስኻ ዲኻ? እስኻ'ውን? እስኻ'ውን መጺእካ? ዘገርም እዩ።"*

*"እንዴ ዶክተር ጌታቸው አንተ ነህ? አንተም? አተም መጣህ? የሚገርም ነው።"*

ሲሉ ይታየኛል። እንግዲህ ከሁለት ሰዓቱ ውይይት ዋናው አንኳሩና ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ይህ ነበርና <u>**አስምሬ አድምቄ**</u> አጉል ነው! ብያለሁ። ይኸው ነው በቃ!

የኤርትራን ጉዳይ በተመለከተ መታየት ያለባቸው በርካታ ጉዳዮች እንዳሉ ቀደም ብዬ በበፊት ጽሁፌ ጠቀስ አድርጌሃለሁ። በሀገራችን ታሪክ ወያኔ የሀገሩን አንድ ክፍል የመገንጠል ዕውቅና ይሰጥልኝ ብሎ ለተባበሩት መንግስታት ያቀረበ ጉደኛ መንግስት ነው። ሻቢያም *"ትግላችን ቅኝ ከያዘችን ኢትዮጵያ ነፃ መውጣት ነው"* በማለት ያደረገው የትጥቅ ትግል ሰምሮለትና በኃያላን መንግስታት አጋሽነት የይስሙላ *"ባርነት ወይስ ነፃነት"* ምርጫ ሆኖ ቀርቦ ማንም አዕምሮ ያለው ባርነትን አይመርጥምና የግንጠላ ከበሮ ተደለቀ። ይህንን በወቅቱ የነበሩ ተቃዋሚ ኃይሎች በነበራቸው የጋራ ስብስብ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ) አማካይነት ለዓለም መንግስታት የተቃውሞ ድምፃቸውን ማሰማታቸው የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው።

*በመሆኑም ዛሬ ግንቦት 7 ለሻቢያ የሰጠው እውቅና ኢትዮጵያ ቅኝ ማድረጓን ከመቀበል የዘለለ አይደለምና ነው ተቃውሞው። የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉዳይ ወደፊት ጥሩ መንግሥት ቢመጣ እንኳ ወሳኙ ሕዝብ ነው። ለዚህም ነው ሪፈረንደም* (ሕዝበ ውሳኔ) *የሚባለው። እንኳን ትግል ላይ ያለ የፖለቲካ ድርጅት ይቅርና በሕዝብ ምርጫ ሥልጣን የያዘ መንግስት እንኳ ሊወስን ዕድሉን የሚሰጠው ለሕዝብ ነው። አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ከሚያስተዳድሯት **ኤርትራ ጋር የሚደረግ ስምምነት ከሌላ ፖለቲካ ድርጅቶች ጋር እንደሚደረግ በጋራ ጠላት ላይ ትብብር መታየት የለበትም።***

*የኤርትራ ጉዳይ አሁን* 24 *ዓመት አስቆጥሯል መተውና እንደገና ኤርትራን እንደሀገር ተቀብለን መልካም ግንኙነት መመስረት አለብን ከተባለ እንኳ አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝብና ማንንም ሳያገል ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በቅድሚያ በጋራ መምከር የሚገባቸው ጉዳይ ነው።* በዚህ ፀሐፊ አስተያየት ***ዴሞክራቲክ ሥርዓት በሀገራችን ተገንብቶ ሕዝብ የመረጠው መንግሥት በሀገራችን ቢመሠረት እንኳ ከኤርትራ ጋር ቀና ግንኙነት ለመፍጠር በቅድሚያ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ "ግርግር ለሌባ ያመቻል" እንዲሉ ያለ አግባብ የተወሰደው አሰብ ለኢትዮጵያ መመለስ አለበት። አሰብ በመለስና ወያኔ ልግስና ለሻቢያ የተሰጠው በዝርፊያ ነውና ቀና ግንኙነት ከኤርትራ ጋር መታሰብ ያለበት እደግመዋለሁ አሰብ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለኢትዮጵያ ከተመለሰላት በኋላ ነው።***

*ዶ/ር ጌታቸው የትላንቱን ማስታወስ እንደማይፈልጉ ኢሜል አርገውልናል። በልጅነታችን ጀምሮ የታሪክ ትምህርት እየተባለ አድገንም የምንማረው እኮ ያለፈ ታሪካችን አውቀንና በርካታ ትምህርት ወስደንበት ዳግም ስህተት እንዳንሰራ ነው። እንደውም ለተደጋጋሚ ስህተት የሚጋብዘን የሀገራችን ታሪክ በደንብ ባለመፃፉና ታሪካችንን በሚገባ ባለማወቃችን ነው።*

*ዶ/ር ጌታቸው የፃፍኩበትን ጉዳይ አቅጣጫ ለማስቀየር ኢሕአፓነቴን ጥያቄ ውስጥ ቢያስገቡም ኢሕአፓ በኤርትራ ጉዳይ ታሪክ ያስመዘገበ ፓርቲ ነው። ኢሕአፓ በጅምር የፖለቲካ ፕሮግራሙ "የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከመገንጠል" ያላቸውን መብት ቢቀበልም በምንም መልኩ የኤርትራን የቅኝ ግዛትነት ጥያቄ ሳይቀበል በአቋሙ በመጽናቱ በሻቢያ መከራን የተቀበለ ፓርቲ ነው። ጅምር የሠራዊት አባላቱን ይለፍ ሰጥተው ወደ ፍልስጤም እንዲሰለጥን ካደረጉ በኋላ እና ሥልጠናው አብቅቶ ወደ ቤዝ ክልሉ አሲምባ እንዳይገባ ሥልጠና የወሰደውን አስኳል የኢሕአፓ ሠራዊት አካልን "የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ መሆኑን ካልተቀበላችሁ" ብለው አግተው መያዛቸው የተዘገበ ታሪክ ነው። ከዚያም ለማንም ህልውናውን የሚሸጠውን ወያኔን አጠናክረውና አደራጅተው የኢትዮጵያን አንድነት ለመበታተን ከተፈለገ ኢሕአፓ መጥፋት አለበትና ዋናውን ጥቃት ከበስተጀርባ ያደርጉ የነበሩት ወያኔና ሻቢያ እንደነበሩ የሚፃፈው ታሪክ አስተማሪ ካልሆነ ችግር አለ ማለት ነው።*

*ይህ ደግሞ የሚያሳየን እንደ ሻቢያ ያለ በተንኮልና በመሰሪነት የታወቀ ድርጅት ግንቦት* 7 *እና ሌሎች ድርጅቶችን ሲያስጠጋ ድርጅቶቹ ለአባላቶቻቸውና ለሚታገሉለት ሕዝብ ግልጽ አያርጉት እንጂ የሚዋዋሏቸው ውሎች፣ የሚጫንባቸው ቅድመ ግዴታዎች እንዳሉ ለማንም*

ግልጽ ነው። ሻቢያ የአሰብ ጉዳይ እንዳይነሳ እነኚህን ኃይሎች ለቀጣይ መንግስትነትም ሊጠቀምባቸው ይፈልጋል። ሻቢያ ከአስቀመጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ *"ስለ አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ጥሩነት፣ ዴሞክራት መሪነት በኢሳት ቴሌቪዥን መናገር፣ ማቅረብ፣ ጉብኝት ወደ ኤርትራ በመሄድ ስለ አቶ ኢሳያስ ቅስቀሳ ማካሄድ"* አንዱ ነው። በቀጣይነት ሲምፖዚየም ብሎ ጉዳዩን ማራገብ፣ ኢትዮ-ኤርትራ የጋራ ባህላዊ ጨዋታ በማለት በሀገርና ሕዝብ ላይ መጨፈር፤ በሜሪላንድ የታቀደው ስምፖዚየም ስኬታማ ቢሆን በአሜሪካን በየስቴቱ ከዚያም በአውሮፓና በሌሎች እየተዞረ በሻቢያ ስም ገንዘብ መሰበስብ። ይህ ነው ትግል!

ሻቢያ/ወያኔ የኦሮሚያ መንግስት ተመስርቶ፣ ምሥራቅ ሱማሌ መንግሥት ተመሥርቶ፣ ትግራይ ትግሪኝ መንግሥት ተመሥርቶ፣ አማራውና ሌላው ብሔር ብሔረሰብ እየተቀጠቀጠና ሰላም እያጣ ኢትዮጵያ እንድትበታተን የፈጠራቸው መንግስታት የበላይ ተቆጣጣሪ ለመሆን ያለው ቅዠታቸው ባይሳካ እንኳ በሀገራችን ላይ በየአቅጣጫው ለጥፋት የተዘጋጁ ኃይሎችን በመርዳትና በመንከባከቡ ያላባራ ጉዞው እየሆነና እየታየ *"ሻቢያን እንደወያኔ መታገል የሚገባን የኢትዮጵያ ጠንቅ ነው"* በሚል ከተለያዩ ፖለቲካ ድርጅቶችና ግለሰቦች የሚቀርቡ ቅሬታዎችንና ተቃውሞዎችን *"ለምን ሰምተን"* ትግሉን ጎጂ እንጂ ጠቀሜታ የለውም።

# Re: Your garbage on Aiga Forum

Thursday, May 14, 2015 12:16 PM
From:
"Getachew Begashaw" <getachew.begashaw@yahoo.com>
To:
"Nesibu" <alulla2@yahoo.com> "

Dear Alem,
As much as I am impressed with your eloquent argument in rejection of any alliance with shabia, I am equally puzzled how you missed the big point, the issue for my reaction. I am not debating on the shabia matter. I am presenting to you the deliberate and abhorrent distortion of my statement by the snippet he purposely misused as if I am saying those words in support of working with shabia. That is a lie; it's a deliberate misrepresentation that is liable. Please tune to my interview on the footage 30:00 to 37:00. You will get the whole story. I said those words in relation to the anti-Ethiopia nature of the TPLF (as elucidated by their creator, Mr. Isayas Afeworki) and doubting about those who are still expecting marvels from the TPLF. This person ascribed those words of mine to his imagined argument in support of allying with shabia. What this person did has nothing to do with a dignified discourse on the thread of the merits and demerits of working with shabia. It was just a pile of garbage peppered with sleazy innuendos, insults, and defamation – much devoid of any substance worth considering. That was the issue you needed to be clear first, and then invite us to discuss on the other issue of your interest which I have no problem with. Although I don't think this is the appropriate fora for a discussion of this nature, I am more than willing to give my considered opinion without any prejudice. Even better, the conference I participated on recently, May 9-10, has resolved to host another conference that is entirely dedicated to this topic – Ethio Eritrea relations. I am not a prisoner of our ugly past nor the history that follows it. Today's Ethiopian realities will have to be discussed and understood by what we have on the ground today, not yesterday.I am giving you heads up so that all interested could prepare to present their findings and interpretations; not such a stumpy merit-less chatters like the one presented by this individual. I am not interested to continue with issue anymore, because there are many more important matters we all can attend to. I don't have to waste my time with such pitiful souls crying for attention beyond righting the record. That is what I did, and it stops here. Thank you for your attention and engagement.
Getachew

በመጨረሻም ለዶ/ር ጌታቸውም ሆነ ለሌሎች የምለው ቢኖር በሀገራችን ጉዳይ ያገባናል ብለን የምንጽፍ፣ በተለያየ መገናኛ አውታሮች (ፓል ቶክ፣ ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣ፣ መጽሔት ወዘተ) የምንቀርብ ምንጽፍ፣ በሕዝባዊ መድረኮች የሚቀርቡ በድርጅት ደረጃም ሆነ በግለሰብ ለምትይዟቸው አቋሞች ድጋፍ እንዳላችሁ ሁሉ ሚቀርብባችሁን ተቃውሞ ለማስተናገድም ሆነ አግባብ ያለው መልስ ለመስጠት ትዕግስቱ ሊኖራችሁ ይገባል እላለሁ። በተለይ አሁን አሁን እየተንጸባረቀ ያለ ይበልጡን በውጭው ዓለም አንድ ችግር አለ። ዶክተር ተብሎ የሚጽፍና ለውይይት የሚቀርብ የሚለው ሁሉ መሬት ጠብ የማይል ተደርጎ ሲወሰድ ያሳዝናል። ማንም በተማረበት የሙያ መስክ ይከበራል፣ አስተዋጽዎ ያደርጋል። በፖለቲካው መስክ ግና ይለያል። ከዛሬ ትውልድ ልጆች ገና በሁለተኛ ደረጃ ያሉ ስለ ሀገራችን ድንቅ ትንታኔ የሚሰጡ፣ ጽሁፍ የሚያቀርቡ እንደሚኖሩ መገመት ይኖርብናል። ዓፄ ዮሐንስ መተማ፣ ዓፄ ቴዎድሮስ መቅደላ ለሀገር የተሰዉት፣ ዓፄ ምንልክ ዐድዋን በድል ተወተው የሀገር አንድነት ያስከበሩት ዶክተር ተብለው አይደለም። አንድ ዶክተር የሀገሪቷን ሁኔታ አስመልክቶ ፖለቲካው መድረክ ላይ ሲቀርብ/ስትቀርብ እራሱን/ሷን እንደ ባለ

ሙያተኛ መቁጠር ሳይሆን ያለበት/ባት እንደማንም "ተራው ሰው" መሆን ይገባል። ምክንያቱም የሚናገረው የሚጽፈው፣ የሚነጋገረው፣ የሚፃፃፈው "ከተራው" ወገኑ ጋር ነውና ምሁርነቱ ይበልጥ የሚሰራው ለሙያ መስኩ ቢሆን ይመረጣል። ዶክተር ነኝና የፃፍኩት፣ ያልኩት ሁሉ ተቀባይነት አለው በማለት "መነገኝ" አለማድረጉ ይመረጣል። አይፃፉ፣ አይናገሩ እንጂ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጆሮዎች እያገናዘቡ እንደሚሰሙ ብቻ ሳይሆን እንደሚያደምጡ፣ ሚሊዮን ዓይኖች አንብበው እንደሚረዱ መጠበቅ አግባነት አለው።

በዛሬው ጽሁፌ አሁንም ከዶ/ር ጌታቸው ሚጠበቅባቸውን ምሁራዊ ትንታኔ እየጠበቅሁ በዕድሜም በዕውቀትም እጅግ የሚበልጡኝን አሉላን/ነሲቡን የስድብ ቃላት በማኅሮጎድጎድ ሌላ ሦስተኛ ወገን እንዲታዘብዎት ኳሱን ከማቀበል ተቆጥበው በሳል ጽሁፎን እጠብቃለሁ። የሰው ልጅ ፍጹም አይደለምና እኔም ተሳስቼ ከሆነ ይቅርታ ታላቅነት ነውና አይፍሩት። በስህተት ላይ ስህተት መደረቡ ነው ለብዙዎች ችግር የሆነውና ቆም ብለው ቢያስቡበት ጥሩ ነው እላለሁ። አይ ካሉም የሚደርሰኝን የክስ ጥሪ እጠባበቃለሁ።

በቅርብ የፃፍኩትንና ለአንባቢያን ያቀረብኩት *"ፍፁም ነው እምነቴ የከፍተኛ 15 ቀይ ሽብር እውነተኛ ታሪክ"* መጽሐፍ ላይ ረቂቁን በማንበብ ስለ መጽሐፉና ስለ እኔ የሰጡት አስተያየት መጽሐፉ ላይ የታተመ *"ዛሬ አሉላን አድራሻህ ወያኔ ነው"* ሲሉ አሁንስ … አይደል?

በሜሪላንዱ ከ May 9-10, 2015 በተካሄደው ስምፖዚየም እውን የሀገሮን የእምዬ ኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ገፋ አድርገው በኤርትራው ሲታጀቡ ምን ይሰማዎታል? (የፎቶው ምንጭ ጌታቸው ረዳ ጽሁፍ አሲምባ ድረ ገጽ http://www.assimba.org/Articles/Teqawami_Mediawoch_LeEthiopia_Hizb_Yeqomu_Nachewwoy.pdf)



ቸር ይግጠመን

ነሲቡ ስብሐት/አሉላ (alulla2@yahoo.com)

ግንቦት 7 ቀን 2007 ዓ.ም